# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ጥቅምት 3 ቀን 2005 ዓ.ም**

**የመለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን ከቤተ መንግስት አልወጣም አለች፤የወያኔ ባለስልጣኖች ከጀርባዋ ያሉ መሆኑ ታወቀ**

**ሠራተኛው የሶስት ወር ደሞዝ በአንድ ዓመት እንዲያዋጣ ሊገደድ መሆኑ ተጠቆመ፤**

**መዋጮውም ለመለስ ቤተሰብ መኖሪያ ቤት ማሰሪያ፤ለመለስ ኃውልት ማስገንቢያ፤ ለአባይ ግድብ ግንባታ በሚል መሆኑ ታወቀ፤**

**ኦህዴድ እራሱን ያጠራል ቢባልም ሳይሆን በመቅረቱ በወያኔ ቡድን ውስጥ ከፍተኛ ድንጋጤ ፈጥሮዋል፤**

**የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትሩ ጁኔዲ ሳዶ ከስራ አስፈጻሚነቱ ተባረረ፤**

*ለ21 ዓመታት ሀገሪቱን እና ህዝቡዋን ሲያምስ የኖረው የወያኔው ቡድን መሪ መለስ ዜናዊ ህይወቱ አልፎ በምትኩ የደቡቡ ተወላጅ ኃይለማርያም ደሳለኝ ስልጣን ከያዘ በሁዋላ ህወሀቶች ቀዘቀዙ የሚል ሆን ብሎ የሚናፈስ ወሬ ቢኖርም በአሁኑ ሰዓት ከመጋረጃው ጀርባ ሆነው ሀገሪቱን እየመሩና እያሽከረከሩ ያሉት እነሱ መሆናቸው እየተነገረ ይገኛል።*

*ህይወቱ ካለፈ አንድ ወር ከ15 ቀን የስቆጠረው የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ከህወሀቶች ጋር በመሆን ከቤተ መንግስት ላለመልቀቅ እያነገራገረች መሆኑ ታወቀ። ለአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ የቤተ መንግስቱን መኖሪያ ቤት አስረክባ እንድትወጣ ከ15 ቀናት በፊት በደብዳቤ ተገልጾላት የነበረ ቢሆንም የመለስን የ80 ቀን መታሰቢያ ሳላከብር ከዚህ ግቢ አልወጣም እያለች መቆየትዋን የገለፀው የደረሰን ጥቆማ የእስዋን ሀሳብ የሚደግፉ*

ህወሀቶችም አብረው አቁዋም ይዘው እንደነበርና  አሁን ያለው የኃይለማርያም የደህንነት ጥበቃ አስጊ በመሆኑ በአስቸኩዋይ ለቅቃ እንድትወጣ የሚያስገድድ ደብዳቤ እንደደረሳት ለማወቅ ተችሎዋል።

ብስራት ገብርኤል ተብሎ በሚጠራው ሰፈር ውስጥ ሲኖር የነበረው ኃይለማርያም ደሳለኝ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ከተሾመበት ዕለት ጀምሮ ልዩ ጥበቃና የደህንነት ውጠራ በመጠናከሩ የአካባቢው ኑዋሪዎች እንደልባቸው መንቀሳቀስ የተቸገሩ ከመሆኑም በተጨማሪ ወደ ስራ ሲገባም ሆነ ሲወጣ በሚደረገው አጀብ መንገድ እየተዘጋጋ እንቅስቀሴዎች ሁሉ በመታቀባቸው ምክንያት በአስቸኩዋይ ወደ ቤተ መንግስት እንዲገባ ቢፈለግም በአዜብ አሻፈረኝ ባይነት በህወሀቶች ደጋፊነት እስከ ዛሬ ተግባራዊ ሲደረግ እንዳልቻለ ከቤተ መንግስት የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

እጅግ ዘመናዊ የሆኑ ሶስት የተለያዩ ሰፈሮች የሚገኙ ቪላዎችን መርጣ እንድትገባ ከ15 ቀናት በፊት ጀምሮ ጥሪ ቢደረግላትም ቤቶቹን የማየትና የቤተ መንግስቱን መኖሪያ ለቅቃ የመውጣት ፍላጎት እንደሌላት የገለፀው የደረሰን ጥቆማ ከውሳኔዋ ጀርባ ቱባ ቱባ የህወሀት ባለስልጣናት አብረው እንደሉም ገልጾዋል።

የህወሀት አክርካሪ ተመትቶ አበቃለት እየተባለ ቢናፈስም በአሁኑ ሰዓትም ስልጣኑን የአንበሳውን ድርሻ የያዙት ህወሀቶች መሆናቸውን የተለያዩ መስሪያ ቤት ሰራተኞችም በንዴት እየገለጹ ይገኛሉ።

ይህ የተነገረው ሰሞኑን በወያኔ መከላከያ ሚኒስትር ስር የሚተዳደረው ብረታ ብረትና እንጅነሪንግ የተባለው አምራች ኩባንያ ሲቪል ሰራተኞች ባደረጉት ግምገማና ውይይት ላይ መሆኑም ታውቆዋል።

በህወሀቱ ብ/ጄ/ል ክንፈ ዳኘው የሚመራው ይሄው ግዙፍ ኩባንያ ሲቪል ሰራተኞቹ ባደረጉት ግምገማ ላይ በተነሳ ውይይት የመምሪያ ኃላፊዎች የሆኑ መሀንዲሶች ከአግባብ ውጭ ትዕዛዝ እንደሚደርሳቸውና ትዕዛዙም ህግን ያልተከተለ ከመሆኑም በተጨማሪ ለማስፈፀም እንደማይገደዱ በመግለጽ የህወሀት የበላይነት ያከተመ መስሎን ነበር አሁን ግን ስንረዳ የበለጠ ተጠናክሮ የመጣበት ነው ሲሉም በምሬት ሲናገሩ መደመጣቸውን ከስብሰባው ተሳታፊዎች የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

በኩባንያው አስተዳዳሪ ብ/ጄ/ል ክንፈ ዳኘው መሪነት  ባለፈው ሳምንት በተደረገው የሰራተኞች ግምገማ ላይ ሰራተኞቹ እንደልባቸው የመሰላቸውን አስተያየት እንዳይሰጡና ሀሳባቸውን እንዳይገልጹ በህወሀት በረሀ አመጣሽ መኮንኖች ሲታፈኑ ቢቆዩም እድሉን ያገኙ ጥቂት መሀንዲሶች ግን በግልፅ በስርዓቱ ላይ ያላቸውን ጥላቻ ማስቀመጣቸውን ከደረሰን ዜና ማወቅ ተችሏል።

በተለይ አንድ የኩባንያው የቴክኒክ ክፍል ሰራተኛ የሆነ ሲቪል መሐንዲስ እንዳለው ከሆነ በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ ውስጥ የብሔር ስብጥር አለ ተብሎ የይስሙላ እየተነገረ ቢሆንም ከዚህ መስሪያ ቤት ጀምረን ወደ ላይ ያሉትን ብንመለከት በሙሉ የህወሀት ሰዎች ብቻ መሆናቸውን እንረዳለን። ስለዚህ በእንዲህ ባለ መልኩ ከሚመራ ድርጅትም ሆነ ቡድን  ለውጥ መጠበቅ ከቶ አይቻልም በማለት የገለጸ

ሲሆን የእሱን ንግግር ተከትሎ በስብሰባ አዳራሹ ውስጥ የተገኙት በሙሉ በጭበጨባ ሲያስተጋቡ የስብሰባው መሪ በድንጋጤና በንዴት ጠረጴዛ እየቀጠቀጠ ሲያስፈራራ እንደነበር ታውቆዋል::

በዚህ መስሪያ ቤት የተደረገው ስብሰባ ዋነኛ አጀንዳው የስራ እንቅስቃሴን መመልከትና መገምገም..... ስርዓቱ ያመጣውን ለውጥ ማድነቅ እና የተለያዩ ሀገራዊ መዋጮዎችን ማጽደቅ የሚሉ የነበረ ቢሆንም ሰራተኛው ባሰማው ተቃውሞ እና ባቀረበው ቅሬታ ምክንያት ስብሰባው ያለ ውሳኔ መጠናቀቁ ታውቆዋል::

በዚሁ ስብሰባ ላይ ዋነኛ መነጋገሪያ ሆኖ የነበረው ሌላው አጀንዳ ሙዋቹ መለስ ዜናዊ በህይወት ዘመኑ መኖሪያ ቤት ያልሰራና አንዳችም ሳንቲም ያላፈራ በመሆኑ ቤት መስሪያ የሚሆን የአንድ ወር ደመወዛቸውን እንዲያዋጡለት የህወሀቱ ብ/ጄ/ል ጄኔራል ክንፈ ዳኘው እንደ ትዕዛዝ ቢናገርም ሰራተኛው በአንድ ድምጽ ኑሮ ከብዶናል አንችልም የሚል መልስ መስጠቱ ታውቆዋል::

ደብረዘይት (ቢሾፍቱ) ውስጥ የሚገኘው ከባድ መኪና መገጣጠሚያ የቲክኒክ ክፍል ኃላፊ የሆነው ኢንጅነር ህዝቡ ኑሮ ከብዶታል የወር ደመወዝ እንዲቆረጥ ከመወሰኑ በፊት በደንብ ይጤን በማለት የሰራተኛውን ሀሳብ አጠናክሮ በመድገሙ ስብሰባውን ሲመራ የነበረው የህወሀቱ ጄኔራል በብስጭት ሰራተኛውን ታሳምጻለህ በሚል በወታደራዊ ፖሊስ ከአዳራሹ እንዲባረር ማድረጉንም ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል::

እንደ ደረሰን ዜና ከሆነ በወቅቱ መሀንዲሱ አስተያየት ሰጥቶ ከመጨረሱ በፊት ስብሰባውን የሚመራው ይሄው የህወሀት ቱባ ባለስልጣን አስፀያፊና ከኢትዮጵያዊ ባህል ጋር የማይሄድ እጅግ ወራዳ ስድብ በመሳደቡ በአዳራሹ ውስጥ ያሉ ሰራተኞች በከፍተኛ ሁኔታ ሲያጉረመርሙ የነበረ መሆኑ ታውቋል::

መለስ በስልጣን ላይ እያለ ምንም ሳንቲም ስላልነበረው ለልጆቹ መኖሪያ ቤት መስሪያ የአንድ ወር ደሞዛቸውን፤ለመለስ ኃውልት ማሰሪያ የአንድ ወር፤እሱ ያስጀመረውን የአባይ ግድብ ማስጨረሻ የአንድ ወር በማለት የሶስት ወር ደሞዛቸውን በአንድ ዓመት በግዳጅ እንዲሰጡ ጄኔራሉ ትዕዛዝ ቢሰጥም ሰራተኛው ሀሳቡን ሳይቀበለው ስብሰባው ሊበተን እንዳቻለ የደረሰን ጥቆማ ገልጸዋል::

በኩባንያው ውስጥ የተለያዩ አምራች ድርጅቶች የሚገኙ ሲሆን በሙሉ ኃላፊነት ላይ የተቀመጡት የሕወሀት በረሀ አመጠሽ መኮንኖች የሆኑና ከያለበት ዲግሪና ዲፕሎማ የተሰጣቸው ነገር ግን ማንበብ መጻፍ የማይችሉ በመሆናቸው የድርጅቱ ሰራተኛ እየተበሳጨ ከመሆኑም በተጨማሪ ብዙ መሐንዲሶች በንዴት ስራቸውን እየለቀቁ እንደሚገኝ ከስፍራው የወጣው ጥቆማ አብራርቶዋል::

በመከላከያ ስር ያሉ አምራች ድርጅቶች በህወሀት አመራሮች የሚመሩ ከመሆናቸውም በላይ በተለያዩ ሰንካላ ምክንያቶች የህዝብ ሀብት በአበል ስም እየዛቁ እና እየሰረቁ ሀገሪትዋን ባዶ ለማድረግ ቆርጠው የተነሱ ይመስላል ሲሉም ሰራተኞቹ በብስጭት ሲገልጹ ተደምጠዋል::

በስብሰባው ላይ ህዝቡ ኑሮ ከብዶታል ብሎ የተናገረው መሐንዲስ ከሁለት ቀናት በሁዋላ ከመኖሪያ ቤቱ በደህንነት ታፍኖ ወዳልታወቀ ስፍራ ተወስዶ የታሰረ ሲሆን ከባድ ድብደባ ሳይደርስበት እንደማይቀር ለቤተሰቦቹ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ስጋታቸውን እየገለጹ ይገኛሉ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔ አንዱ ክንፍ የሆነው ኦህዴድ ለ15 ቀናት በአዳማ (ናዝሬት) ገልማ አባገዳ አዳራሽ ውስጥ ሲያደርግ የነበረው የማዕከላዊ ኮሚቴ ዝግ ስብሰባ ያለ ውሳኔ መጠናቀቁ በወያኔ ውስጥ ሌላ ቀውስ ሊፈጥር እንደሚችል እየተነገረ መሆኑ ተጠቆመ::

ከመስከረም 15 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 29 ቀን 2005 ዓ.ም ለ15 ተከታታይ ቀናት ማዕከላዊ ኮሚቴው ዝግ ስብሰባ እና ግምገማ አድርጎ በተለይ የስልጣን ይገባናል ጥያቄ ያነሳሉ በሚባሉት አመራሮች ላይ ውሳኔ ያሳልፋል ተብሎ ሲጠበቅ ከዚህ ቀደም ከስራ አስፈጻሚነታቸው ተነስተው በነበሩት ምትክ ብቻ ሹመት ሰጥቶ መጠናቀቁ በወያኔ ውስጥ ሌላ የፖለቲካ ቀውስ ሊፈጥር ይችላል ተብሎ ከፍተኛ ስጋት ማሳደሩ ተጠቁሞዋል::

የጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ቦታ ለእኛ ይገባናል እያሉ ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ የኦህዴድ ካድሬዎችን ሲያስተባብሩና ሲያነሳሱ ነበር በተባሉት የኦህዴድ ስራ አስፈጻሚ አባላት ላይ የማዕከላዊ ኮሚቴው ዝግ ስብሰባ አድርጎ እርምጃ ይወስድባቸዋል ተብሎ ሲጠበቅ ያለ አንዳች ተግሳጽ እና ውሳኔ ማጠናቀቁ ኦህዴድ ውስጥ ጥያቄው በአብዛኛው ተቀባይነት እንዳለው የሚያሳይ በመሆኑ ስብሰባው ውሳኔ ሳይሰጥበት ሊጠናቀቅ እንደቻለም ታውቆዋል::

በኦህዴድ ከፍተኛ ካድሬዎች እየተነሳ ያለው የጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ቦታ ጥያቄ ያስደነገጣቸው የህወሀት በረሀ አመጣሽ ባለስልጣናት ድርጅቱ ውስጡን እንዲያጠራ ትዕዛዝ ሰጥተው በአዳማ (ናዝሬት) ግምገማና ስብሰባ ሲያደርግ ቢቆይም በአብዛኛው የማዕከላዊ ኮሚቴ አባሎች ዘንድ ጥያቄው ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ አንዳችም የጎላ እርምጃ ሳይወስድ በሌሎች አጀንዳዎች ላይ ብቻ ሲወዛገቡ መሰንበታቸው ታውቆዋል::

በድርጅቱ ውስጥ የፖለቲካ ሹም ሽር ሊደረግ ይችላል ተብሎ በህወሀቶች እና በብአዴኖች ዘንድ በጉጉት ሲጠበቅ የነበረ ቢሆንም እንዳሰቡትና እንደጠበቁት ሳይሆን ቀርቶ ያለ ውሳኔ ማጠናቀቁ በወያኔ ቡድን ውስጥ ግዜ ጠብቆ የሚፈጠር ችግር እንደሚኖር እየተነገረ ይገኛል::

የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በህይወት እያለ የአመራር ውስንነት ታይቶባቸዋል ተብሎ ከስራ አስፈፃሚነት ቦታቸው ተነስተው በነበሩት የክልሉ የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ ለማ መገርሳ....የክልሉ የግብርና ቢሮ ኃላፊ ዘላለም ጀማነህ.....በፌዴራል የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር ደኤታ አለማየሁ እጅጉ ምትክ ሌሎችን ከመሾም ባለፈ አንዳችም ውሳኔ አለመስጠቱ በተለይ በህወሀት በረሀ አመጣሽ ባለስልጣናት ዘንድ ድንጋጤን እንደፈጠረም ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

በዚሁ ስብሰባ ላይ አንዱ አጀንዳ የነበረው የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትሩ ጁኔዲ ሳዶ ጉዳይ ሲሆን ግለሰቡ በተወለድኩበት አካባቢ የወላጅ እናቲን ኑዛዜ ለመፈፀም ስል አሰራሁት ካለው መስጊድ ጋር በተያያዘ ከሳዑዲ ዓረቢያ ኤምባሲ አምባሳደር እና ሌሎች ሰራተኞች ጋር የተሳሰረ ግንኙነት በመፍጠሩ የተነሳ ጥልቅ ግምገማ ተካሂዶበት ከኦህዴድ ስራ አስፈጻሚነት ቦታው ተነስቶ ተራ አባል እንዲሆን

ውሳኔ ተላልፎበታል፡፡

ይሄው የወያኔ ተላላኪ ባለስልጣኑ ጁኔዲ ሳዶ በነሐሴ ወር ውስጥ ባለቤቱ ከሳዑዲ አረቢያ ኤምባሲ 50 ሺህ ብር እና 500 የሚሆን ቁርዓን መጽሀፍ ይዛ ስትወጣ ተያዘች ተብሎ ማዕከላዊ ምርመራ ከታሰረች በሁዋላ ለህዝቡ በበተነው የአድኑኝ ግልጽ ደብዳቤ የተነሳ በኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ተነስቶ ግለሂስ እንዲያወርድ ተደርጎ ከስራ አስፈፃሚነት እንዲወገድ የተወሰነ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

ጁኔዲ ሳዶ ከዓመታት በፊት በስሙ ከዐረብ ሀገራት ጠቀም ያለ ገንዘብ እየተላከለት እንደሚቀበል በመረጃና ደህንነት ቢሮ ጭምር የሚታወቅ እንደነበር ደጋግመን ስንገልጽ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በሀገሪትዋ በተቀሰቀሰው የሙስሊሙ እምነት የመብት ጥያቄ በመደናገጥ ግለሰቡንም ከዚሁ ጋር በማያያዝ ባለቤቱን ለእስር መዳረጋቸው ጉዳዩን የሚከታተሉ ወገኖች ሲገልጹ ተደምጠዋል፡፡

ባለቤቱ ማዕከላዊ ምርመራ እስር ቤት ከገባችበት ነሐሴ ወር አጋማሽ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ፍርድ ቤት ያልቀረበች መሆኑን በግምገማው ላይ የተናገረው ጁኔዲ ሳዶ ሳላውቅ በብስጭት ስሜታዊ ሆኜ ለህዝቡ የአድኑኝ ደብዳቤ መበተኔ ጥፋተኛ ያደርገኛል ስለሆነም ወደፊት ስራ ሰርቼ ድርጅቱን እክሳለሁ በማለት ግለሂስ ማውረዱን ለማወቅ ተችሉዋል፡፡

በዚህም የተነሳ ቀድሞ የአመራር ውስንነት ታይቶባቸዋል ተብለው ከወራት በፊት በተነሱት ሶስት ባለስልጣናት እና ሰሞኑን ከአክራሪ ሙስሊሞች ጋር በተያያዘ በተሰናበተው ጁኔዲን ሳዶ ምትክ የኦሮሚያ የዞን አስተዳዳሪ የሆኑት ተመርጠው የስራ አስፈጻሚነት ሹመት ተሰጥቶዋቸዋል፡፡

በተለያዩ የስብሰባ ወቅቶች ከመለስ ጋር ሙግት የምትገጥመው አስቴር ማሞ በዚሁ የአዳማው ዝግ ስብሰባ ላይ በፌዴራል መዋቅር ውስጥ የነበራትን ስራ አቁዋርጣ ወደ ክልሉ እንድትመለስ የተወሰነ ሲሆን ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ተጠሪነትም እንደተነሳች ታውቆዋል፡፡

ከሁለት ዓመት በፊት መለስ ካቢኔ በዋቀረበት ወቅት የኦህዴድ ሊቀመንበር እና የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት የነበረው አባዱላ ገመዳ ወደ ፌዴራል ሲዛወር የኦህዴድ ካድሬዎች እንዳይዘዋር ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያስሙ የነበረ ቢሆንም አድማጭ አጥተው ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን አሁንም አስቴር ማሞ ወደ ክልሉ እንድትመለስ በተወሰነው መሰረት ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከመንግስት ተጠሪነት ቦታዋ ተነስታ በምትኩዋ የደቡቡ መለስ ጥላሁን የተባለው ግለሰብ መቀመጡ ታውቆዋል፡፡

በስብሰባው ማጠናቀቂያ ላይ ከመለስ በፊት በህመም ምክንያት ሊሞት ነው ተብሎ ብዙ ሲወራበት የነበረው የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት እና የኦህዴድ ሊቀመንበር አለማየሁ አቶምሳ ስልጣኑን ያስረክባል ተብሎ ሲጠበቅ የነበረ ቢሆንም ግለሰቡ በያዘው ስልጣን እንዲቀጥል በዚሁ ውሳኔ ላይ መገለጹ ታውቆዋል፡፡

በመጨረሻም የወያኔ ቡድን ባደረበት ፍርሀት የተነሳ በህዝቡ ላይ ከፍተኛ ጫና እየፈጠረ ከመሆኑም በተጨማሪ በተለያዩ ሰበቦች እያፈሰ ለእስር እየዳረጋቸው እንደሚገኝ የደረሰን ጥቆማ አስታወቀ፡፡

ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ባሉ ቀበሌዎች የሚኖሩ አርሶ አደሮች ላይ በተወሰደ እርምጃ ቁጥራቸው አስር የሚሆኑትን አፍሰው ለእስር መዳረጋቸው ታውቆዋል፡፡

የወያኔ ቡድን መሬት አይሸጥም አይለወጥም ህጉም አይሻሻልም ሲል እንዳልነበር ሰሞኑን እትብታቸው ከተቀበረበት ቀዬ አርሶ አደሮቹ እንዲነሱ እና በግዳጅ ለባለ ሀብት በርካሽ ዋጋ እንዲሸጡ በፖሊስ ሲንገላቱና ሲታሰሩ መሰንበቱ ታውቆዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዙሪያ ከሚገኙት ቀበሌዎች በለገዳዲና በለገጣፎ አቅራቢያ ያሉ አርሶ አደሮች ከአያት ቅድመ አያቶቻቸው ሲተላለፍ የመጣውን..... ለዘመናት በእርሻ ሲተዳደሩበት የነበረውን..... እትብታቸው የተቀበረበትን ቀዬ በአነስተኛ ሂሳብ በግዳጅ እንዲሸጡ ቢታዘዙም የወያኔን ትዕዛዝ አንቀበልም በማለታቸው ህዝቡ ሲንገላታ ከመሰንበቱም በተጨማሪ አስተባባሪ ናችሁ የተባሉ አስር አባዎራዎችን አፍሰው ሰንዳፋ ፖሊስ መኮንኖች ማሰልጠኛ ግቢ እንዳሰሩዋቸውም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት መሬት የህዝብና የመንግስት ነው የሚለውን እራሳቸው ያወጡትንና ያፀደቁትን ህገ መንግስት በመሻር የለገዳዲና የለገጣፎ አካባቢ አርሶ አደሮችን የወያኔ ባለስልጣናት እትብታችን ከተቀበረበት ቀዬ እንድንነሳና በአነስተኛ ገንዘብ ለአንድ የውጭ ሀገር ባለሀብት እንድንሸጥ እያስገደዱን ያለው ድርጊት የሚያሳፍር ከመሆኑም በላይ የሚያሳዝን ነው ሲሉም በንዴት ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

በወያኔ ቡድን ውስጥ መረጋጋት ጠፍቶ ስርዓቱን ለማሰንበት ሲባል በየቀኑ የተለያዩ ዘዴዎችን እየፈጠሩ ባለበት በአሁኑ ወቅት ዜጎች ለዘመናት ከኖሩበት ሀገር እና እትብታቸው ከተቀበረበት ቀዬ እንዲፈናቀሉ የሚደረገው ደባ አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ ወንጀል መሆኑን የሚናገሩት እነኚሁ አርሶ አደሮች በአስቸኳዋይ መሬቱን ለቅቀው ካልሔዱ የከፋ እርምጃ እንደሚወሰድባቸውም ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸው ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

መብታቸውን የጠየቁና ሀብት ንብረታቸውን አናዘርፍም ብለው የተከራከሩትን አስር አባወራ አርሶ አደሮች ህዝቡን እያሳመጻችሁ ያላችሁት እናንተ ናችሁ..... በፀረ ልማት ተግባር ላይ እንዲሳተፍ እየገፋፋችሁት ነው ...... መንግስት ሞቶዋል ብላችሁዋል በሚል ዓርብ መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ.ም ከየመኖሪያ ቤታቸው በኦሮሚያ ልዩ ኃይል እና በፌዴራል ፖሊስ ታፍሰው እየተደበደቡ ሰንዳፋ ፖሊስ ኮሌጅ እስር ቤት የከተቱዋቸው ከመሆኑም በላይ ጠዋት ጠዋት ቀዝቃዛ በተሞላ በርሜል ውስጥ እየተነከሩ እንደሚያሰቃዩዋቸውም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

አርሶ አደሮቹ መሬቱ ከአያት ቅድመ አያቶቻችን ሲተላለፍ የመጣና በቤተሰባችን ኮታ የተሰጠን ከመሆኑም በላይ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ያለን ግብር የምንከፍልበት ስለሆነ እራሳችን እያለማን እንጠቀምበታለን አንሸጥም በማለታቸው በወያኔ ባለስልጣናት ትዕዛዝ እንዲነሱ የተደረገ ሴራ መሆኑን ታሳሪዎቹ ይገልፃሉ፡፡

አቶ መኮንን ተስፋዬ..... አቶ ገመቹ ወርቁ.....አቶ ስዩም አበበ..... አቶ ሲሳይ ለማ.....አቶ ዳዲ ሂርጳ..... አቶ ጌታቸው ተፈራ...... አቶ ድሪባ ጉዳ......አቶ ድሪባ ገመዳ..... አቶ ምትኩ ንጉሱ እና አቶ እንዳልካቸው መንግስቱ የተባሉ አስር አርሶ አደሮችን ሕዝቡን እያሳመጻችሁና ቅስቀሳ እያደረጋችሁ

በመንግስት ላይ ነውጥ ልታስነሱ ነው ተብለው የታሰሩትን አባዎራዎች የሰንዳፋ ወረዳ ፍርድ ቤት እያንዳንዱን በሶስት ሺህ ብር ዋስትና እያስያዙ እንዲለቀቁ ቢፈቅድም ፖሊስ ሌላ ክስ ስላለኝ በሚል እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ ያለቀቃቸው ከመሆኑም በላይ ከቤተሰብ ጋር እንዳይገናኙ በመደረጋቸው ቤተሰቦቻቸውም ለከፋ ችግር ተዳርገው እንደሚገኙ ይሄው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

በቅርቡም በጎንደር እስቲ ውስጥ ህዝቡ የመብት ጥያቄ በማንሳቱ ብቻ ሴት... ወንድ... ህጻን... ሽማግሌ... ሳይል በወያኔ ፌዴራል ፖሊስ ሲደበደቡና ለእስር ሲዳረጉ እንደነበር የዘገብን ሲሆን በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ በሚገኙ ዜጎች ላይም የከፋ ስቃይ እና እንግልት እየደረሰ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡